# አሁንም ጊዜያዊ ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋነኛው ጥያቄው የዲሞክራሲ ጥያቄ ነው። ዲሞክራሲ ማለት ደግሞ በመዝገበ ቃላት ትርጉሙ መሠረት፤ ሕዝባዊ መንግሥት ማለት ነው። ኢትዮጵያ በታሪኳ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት ኖሯት አያውቅም። በሕዝቡ ያልተመረጠ መንግሥት ድግሞ አምባገነን ይባላል። አምባገነን መንግሥት ድግሞ በራሱ ፈቃድ አንድን አገር ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊወስድ አይችልም። ምክንያቱም አምባገነን በራሱ ፈቃድ ራሱን ሊያጠፋ አይፈልግምና። ይህን ለውጥ ማድረግ የሚችለው በለውጡ ተጠቃሚ የሆነው ሕዝቡ ራሱ ብቻ ነው። በአምባገነንና በሕዝባዊ መንግሥት መሃከል ያለው ልዩነት የብርሃንና የጨለማ ዓይነት ስለሆነ ሁለቱም በአንድ ላይ ሊገኙ አይችሉም። ከአምባገነኑ ወደ ሕዝባዊ መንግሥት ሥርዓት የሚደረገው ሽግግር ሥር-ነቀል ለውጥ ይባላል። ብዙውን ጊዜ አብዮታዊ ለውጥ ተብሎ ይጠራል።

ሥር - ነቀል ለውጥ ሲባል በአምባገነኑ አገዛዝ ጊዜ የነበሩትን ሰዎች፤ ባህሎችና ልምዶች መደምሰስ ማለት አይደለም። እንዲያውም ያለመገዳደል ሊመጣ የሚችል ለውጥ ሊሆን ይችላል። ችግሩ ግን አምባገነኑና አድርባይ ባለሟሎቹ ፤ ሥልጣናቸውንና ጥቅማቸውን በሰላም ሊለቁ አለመፈለጋቸው ነው። ስለዚህ የግጭቱ ተጠያቂዎች ሕዝባዊ መንግሥት ጠያቂው ሕዝብ ሳይሆን፣ ሥልጣኑን ለባለቤቱ ሕዝብ አላስረክብም ባዩ አምባገነንና ተከታዮቹ ናቸው።

> "በሰዎች መሃከል የሚቋቋሙት መንግሥታት ሕጋዊ ሥልጣናቸውን የሚያገኙት በተገዢው ፈቃድ (ይሁንታ) ነው። ይህን ዓላማ የሚያጠፋውን ማንኛውንም ዓይነት መንግሥት ፣ የመለወጥ ወይንም የመደምሰስ መብቱ የሕዝቡ ነው"።

ይህ ጥቅስ የኔ አይደለም። አሜሪካኖች በአብዮታቸው የነፃነት አዋጅ መግቢያ (PREAMBLE OF THE DECLARATION OF INDEPENDENCE) ላይ ያስቀመጡት ዝነኛው ታሪካዊ ጥቅስ ነው። መስመሩ ግን የኔ ነው። ይህን ጥቅስ መቀበል የሚቸግረው ሰው፤ ሥልጣን የሕዝብ መሆኑን ከልቡ መቀበል ያስቸገረው ሰው ነው። በነገራችን በጥቅሱ ውስጥ የተጠቀሰው የሕዝብ ፈቃድ (ይሁንታ) የሚገለጸው በሆይ ሆይታ ሰልፍ ሳይሆን፣ በምርጫ ሳጥን ነው። የጥቅሱም እምቡጭ ሃሳብ የመነጨው " THE LEGITIMACY OF ANY GOVERNMENT DEPENDS UPON THE CONSENT OF THE GOVERNED" ከሚለው የታላቁ JOAN LOCKE ጥቅስ ላይ ነው። በአጭሩ በሕዝብ ያልተመረጠ መንግሥት ሕገ ወጥ ነው ማለት ነው።

እንዲያውም እንደእኔ አመለካከት አምባገነን ሕገወጥ ብቻ ሳይሆን የመጨረሻው ወንጀለኛም ነው። ለምሳሌ በዘመናችን ከምናውቃቸው ወንጀለኞች ዋነኛው ሴሪያል (አከታትሎ) ገዳይ ነው ብንል፤ ብዙዋቻችን እንስማማለን። ታዲያ አከታትሎ ገዳይ በሞት እንዲቀጣ የምንስማማበት ዋነኛው ምክንያት ወደ አስርና ሃያ ሰው በመግደሉ አይደለምን? አምባገነን ግን የሚገድላቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ንፁሃን ዜጎች ናቸው። በዛ ላይ አምባገነኑ በሚሠራቸው አይቀሬ የፖሊሲ ስህተቶች ፤ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ዜጎች በጦርነት፣ በረሀብ፣ በስደት ይሞታሉ። ስለዚህም ነው አምባገነን የመጨረሻው ወንጀለኛ ነው ያልኩት። ቢሆንም መግደል ስለማንችል ብቻ እንግደለው አላልኩም። እንዲያውም የሞት ቅጣት የሚባለው ፍርድ ከነጭራሹ መሰረዝ አለበት ከሚሉት ሰዎች ውስጥ ነኝ።

ቢሆንም ግን ለምሳሌ ሕግ አስከባሪው ፖሊሶች ወንጀለኛን በቁጥጥር ሥር ለማስገባት ወንጀለኛው በተገኘበት ቦታ ሲከቡት፣ የተኩስ እሩምታ ቢከፍትባቸውና ጉዳት ቢያደርስ ወንጀለኛውን መግደል እንድሚገደዱ እንገነዘባለን። በተመሳሳዩም ሕዝብ አምባገነኑን ለማውረድና እና በሙብታቸው መሰረት፣ ሥልጣኑን በእጃቸው ለማስገባት በሚያደርጉት ትግል፣ አምባገነኑን የማሰር ፣ የመደብደብ፣ የማሳደድ፣ የመገደል ወንጀል በላያቸው ላይ ቢፈጽምባቸው፣ እና አጸፋውን ቢመልሱ ስህተት ነው ሊባል ይገበዋልን? እዚህ ላይ አስታውሱ የሕዝቡ የሥልጣን ጥያቄ ሕጋዊ ነው። ሕገ-ወጡ አምባገነኑ ገዢ ነው።

የዛሬ 40 ዓመት በኢሕአፓና በደርግ መንግሥቱ ኃ/ማሪያም መሃከል የተደረገው ትግል መታየት ያለበት ከዚሁ አንፃር ነው። ኢሕአፓን ሕጋዊ የሚያደርገው ባነገበው ዋነኛው ጥያቄው ነው። ይህም የኢሕአፓ ዋነኛ ጥያቄ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም ነው። የደርግን አምባገነንነት የሚክድ ካለ የፖለቲካ ሀሁ ያልገባው ስልሆነ፤ ስለዲሞክራሲ ጥያቄ መጽሐፍቶችን ቢያነብ ይሻለዋል።

በርግጥ ይህ የኢሕአፓ ሕጋዊነት እና የደርግ መንግሥቱ ኃ/ማሪያም ሕገ ወጥነት ያልተዋጠላቸው አንዳንድ ሰዎች ሲናገሩ፣ በዚያን ጊዜ ኢሕአፓም ሆነ ደርግ ሁለቱም የሚያቀነቅኑት የነበሩት ሶሻሊዝም ነው። በመሃከላቸው ልዩነት አልነበረም ይሉናል። ነገር ግን በጊዜው ኢሕአፓ ያቀረበው ሕዝባዊ መንግሥት ምስረታ መፍትሄው ሥር ነቀልና አዲስ ዓይነት ፍቱን መፍትሄ መሆኑን ማየት ያቻሉ አይመስልም። በሶሻሊዝም ውስጥ ቢሆንም እንኳን በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት ማቋቋም አዲስ ዓይነት መፍትሄ ነበር። የታንዛኒያውን ኔሬሬ የሶሻሊዝም ሙከራ ማየት እንችላለን። ኔሬሬ በምርጫ ሲሸነፍ ሥልጣኑን አስረክቦ ወደ እርሻው ነው የገባው። በዚያ ላይ ኢሕአፓ ኢትዮጵያ ውስጥ በላብአደር አምባገነንነት ሊመሠረት የሚችለው ሶሻልሊዝም ጊዜ ገና ነው። ይህን ሊያደርግ የሚችለው የላብአደር ቁጥር እጅግ በጣም አነስተኛ ስለሆነ፣ በቅይጥ ኢኮኖሚ ዘዴ ላብ አደሩንና ኢኮኖሚውን ሊያሳደግ የሚችል፣ የውጭ ጥገኛ ያልሆነ ብሔራዊ አፍርተን አሳድገን የምንደርስበት የመጨረሻው ግባችን ነው ብሎ ያምን ነበር። በዚህም ምክንያት ብዙ የኢሕ አፓ መሪዎች ማኦኢስቶች ናቸው ተብለው ይታሙ ነበር። በነገራችን ላይ በጥገኛ ቡርዣ መሪነት ያደገ ኢኮኖሚ ያለው አገር አሁንም አላውቅም። የቻይና እድገት አከራካሪ ነው። እንደ እኔ ግንዛቤ የማኦ ፍልስፍና በቻይና በቻይና እድገት ላይ ትልቅ ሚና ተጫውቷል ባይ ነኝ። ከዚህ በተረፈ በቀዝቃዛው ጦርነት አሰላለፍ ላይ አሜሪካኖች ቻይናን ከሳናቸው ላማሰላፍ ባደረጉበት ጥረት ከቻይና ጋር ያደረጉት ለየት ያለ ግንኙነት ለቻይና እድገት ትልቅ አስተዋጾኦ አድርጓል። ስለዚህ በአጭሩ ኢሕ አፓም ሆነ ደርግ ሁለቱም መመሪያቸን ሶሻሊዝም ነው ቢሉም ቅሉ በሶሻሊዝም ምሥረታ ላይ ያላቸው ግንዛቤ የተለያየ ነው።

በተቃራኒው ደግሞ በሌላ አንድ አገር በካፒታሊዝም ስርዓት ጎዳና ላይ ያለን አምባገነን የሚቃወሙና ለሕዝባዊ መንግሥት (Democracy) የሚታገሉ ግን ካፒታሊዝምን የተቀበሉ ታጋዮች ሊኖሩ ይችላሉ፣ ግን ሁለቱም ለአንድ ሥርአት ነው የሚታገሉት እና ልዩነት የላቸውም ብሎ ሁለቱንም ደምሮ አንድ ላይ ማውገዝ ትክክል አይደለም።

አንዳንድ የፖለቲካ ግንዛቤአቸው ጥልቀት የሌለው ፖለቲከኞች ደግሞ ሲናገሩ፣ ደርግ ሥልጣን ላይ ሊቆይ የቻለው፣ ተማሪ የተባለው ወጣቱ እርስ በርሱ ተከፋፍሎ በመገዳደሉ ነው ይላሉ። ይህ አባባል ከተማሪ

ሰው አፍ ሲወጣ መስማት ያሳፍራል። በየትኛውም አገር ታሪክ ውስጥ የተማረው ወጣት ሰው፣ ጠቅልሎ በአንድ ጎራ ተሰልፎ አያውቅም። ይህ ግንዛቤ የሚመነጨው ሁሉም ወጣት ወይም የተማረ ሰው ለሥር ነቀል ለውጥ ይሰለፋል ብሎ ከመጠበቅ የመጣ ስህተት ነው። የተማረውም ወጣት እንድማንኛውም ህብረተሰብ በፖለቲካ አቋሙ ወደ ግራ ወይንም ወደ ቀኝ ሊያደላና ሊሰለፍ ይችላል። ስለዚህ ሊወገዝ ወይም ሊመሰገን የሚገባው ጠቅላላው ወጣት በደፈናው ሳይሆን፤ ከአምባገነኖች ጎን የተሰለፈው ሊወገዝ፣ ከሕዝብ ጎን የተሰለፈው ደግሞ ሊመሰገን ይገበዋል።

ይህን ሁሉ ሀተታ፣ ወደ ኢትዮጵያ የኋላ 40 ዓመት ታሪክ ሄጄ ያነሳሁበት ምክንያት አለኝ። ባለፈው ሣምንት መጨረሻ በዲሲ እና ሎሳንጀለስ በኢትዮጵያውያን ፊት ቀርበው ንግግር ያደረጉት ዶክተር አቢይ ስለቀሰቀሱት ነው። ዶክተሩ ሲናገሩ እኔ የማካሄደው ለውጥ ጥገናዊ እንጅ ስር ነቀል ለውጥ አይደለም ። ምክንያቱም ስር ነቀል ለውጥ መገዳደል ነው። የዛሬ 40 ዓመት የነበረው የተማረ ወጣት በሥር ነቀል ለውጥ ምክንያት እርስ በራሱ ሲገዳደል ደርግ በሥላጣን ላይ ሊቆይ ችሏል። ስህተቱ የታጋዮች ነው። ቢሆንም ይቅርታ አድርገንላቸዋል ሲሉ የጠቅላይ ሚኒስተር ፍርዳቸውን ስጥተውናል። ከዚህ የባሰ ፍርደገምድልነት ስምቼም አላውቅም። ጥሩነቱ ዋናው ፈራጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጅ እሳቸው ያለመሆናቸውን ነው። ዶክተሩ ኢሕአፓዎች የፃፉዋቸውን ጽሁፎች አንብቤያለሁ ብለዋል። ታዲያ ጽሁፎቹን ካነበቡ በኢሕአፓና በመኤሶን መሃከል ስላለው ልዩነት እንዴት ሳይገባቸው ቀረ? በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ተጽፏል። መንግሥቱ ኃ/ማሪያም አምባገነን ነው ካልን፣ ሕገ ወጥ ነው ማለታችን ነው። ታዲያ በምን ሂሳብ ነው ከመንግሥቱ ጋር የተሰለፉት ምሁራኖች ትክክል የሚሆኑት? በኢሕአፓ ላይ የሚደርሰው እስራትና የግድያ ጥቃት እየተባባሰ የመጣው መኤሶንና ደርግ ግንባር ከፈጠሩ በኋላ አይደለምን?

በጣም ያሣዘነኝ የዶክተሩ ንግግር ግን ዲሲ ላይ ከተቀዋሚ ፓርቲዎች ጋር ባደረጉት ስብሰባ ላይ ከአብዛኛዎቹ ተወካይ ተናጋሪዎች የቀረበላቸው የጉባኤ ምስረታ ጥያቄ ያጣጣሉበት ንግግር ነው። የሰላምና የእርቅ ጉባኤን ጥሪ ሲያጣጥሉት፣ አስታራቂው በዛ፤ ማስታረቅ ቢዝነስ ሆኗል፣ እያሉ ትልቁን አስቸኳይ መፍትሄ አበሻቀጡት። ለነገሩ ጉባኤው ቢጠራ የሕዝቡ ትኩረት ከሳቸው ድስኩር ይልቅ ወደ ጉባኤው እንደሚዞር በቅድሚያ የተገነዘቡ ይመስላል። ጉባዔው ዞሮ ዞሮ የመጨረሻ ዘለቄታዊ መፍትሄ ጊዜያዊ ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት መመስረትን አስፈላጊነት የሚያውጅ ውሳኔ ማሳለፉ የማይቀር መሆኑን ገምተዋል። ስለዚህ የጉባዔውን ጥሪ ማጣጣላቸው አይገርምም። አከታትለውም ስለጊዜያዊ ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት የሰጡት አስተያየት በጉዳዩ ላይ ያላቸው ግንዛቤ ውስን መሆኑን ያሳያል። ዶክተሩ እንዳሉት የተቋሚዎቹ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት ጥያቄ ሃያ ስምንቱን የሚኒስትሮች ቦታ ለመሻማት አይደለም። በርግጥ የሽግግር መንግሥቱ የሚመሠረተው ከጉባዔው ውስጥ በተወጣጡ ስዎች ወይም ደግሞ፣ ጉባዔው በመረጠው ጠ/ሚኒስቴር ከፈለገው ቦታ ባሰባሰባቸው ሚኒስቴሮች የተውጣጣ ሊሆን ይችላል። የጉባዔው ዋና ዓላማ ግን፣ ሕዝቡን ለዋናውና ለተከታታይ ሕዝባዊ ምርጫ ማዘጋጀት ሲሆን ፤ ለዚህም እንዲበጅ ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት የሚያረቅና ሕዝቡን አወያይቶ የሚያፀድቅ የሕግ መንግሥት አርቃቂ ጉባዔ ማቋቋም ነው።

ዶክተሩ እኔ በሽግግር መንግሥት አላምንም ካሉ በኋላ፣ ማንኛውም መንግሥት የሽግግር መንግሥት ነው ብለው ፍርጥ አደረጉት። ትንሽ ቆይተው ደግሞ አይዟችሁ እኔ አሸጋግራችኋለሁ ብለው የተለመደውን የፈዝ ተሰፋ አስጎነጩ። ካነጋገራቸው የምንረዳው የሽግግሩ መንግሥት ሚስጥሩ ያለው ሕዝባዊነቱ ላይ

መሆኑ የገባቸው አይመስልም። ያተኮሩት ጊዜያዊነቱ ላይ ብቻ ነው። የደርግ መንግሥት የሽግግር ጊዜያዊ ወቅትና ሃይል ነበረው። ግን ሕዝባዊ ባለመሆኑ ያው አሸጋጋሪው ጠቅልሎት ቀረ። የወያኔው ሽግግር ከደርጉ ጋር በጣም ተመሣሣይ ነው። ሽግግሩ ለምን ጊዜያዊ መሆን እንዳለበት፣ ለምንስ ሕዝባዊ ሊሆን እንደሚገባው የዛሬ 40 ዓመት ሞቅ ያለ ክርክር በተደጋጋሚ ይደረግበት እንደነበረ አስታውሳለሁ፤ ክህደት ካልሆን በስተቀር በስብሰባው ላይ የነበሩትና እጅ የነሱት አዛንቶች በሙሉ የነበሩበት ስለሆነ ያስታውሱታል።

ዶክተሩ እኔ አሸጋግራችኋለሁ ብለው ሲሉ ፣ መቼም እርሳቸው በነጠላ ብቻቸውን የሚያደርጉት ተግባር እንደሆነ አድርገው የሚገምት ተላላ የለም። የኢሕአደግ ተወካይ እስከሆኑ ድረስ እኔ ሲሉ ከጀርባቸው ያለውን የሾማቸውን ድርጅት ወክለው ነው የሚናገሩት ብሎ መገመት አያዳግትም። በአንድ የዲሲ ስብሰባ ላይ በተቋሚዎች(የሆዳሞች ስብስብ) ፊት ሲናገሩ ፣ እኛ ከሁለት ዓመት በኋላ ለሚመጣው ምርጫ በሰፊው እየተዘጋጀን ነው። ወጣቱን እያደራጀን ነው። እናንተ ተፎካካሪዎችም ከአሁኑ ዝግጅት ጀምሩ ብለው ሲሉ ፣ እኛ ያሉት ኢሕአደግን እንደሆነ ግልፅ ነበር። ታዲያ አንድ ራሱን ለ27 ዓመታት በሙሉ በሥልጣን ፣ በኢኮኖሚና በሰው ሃይል ሲፈረጥም የከረመ ገዢ ፓርቲ በፈቃደኝነት ሥልጣኑን ለህዝብ ያስረክባል ወይ ብለን መጠየቅ አለብን።

ኢሕአደግ ላለፉት 27 ዓመት ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ለረዥም ጊዜ በሥላጣን ለመቆየት ያሰበና ያቀደ መሆኑን የሚያመላክተው ምልክት የኢሕአደግ ህገመንግሥት ነው። ዶክተሩ ስለህገመንግሥት ሲናገሩ ህገመንግሥትና ህልም እንድፈቺው ነው ብለዋል ይባላል። ይህ በእውነቱ የተሳሳተ ማሣሌ ነው። አንድን ህልም ሁለት ህልም ፈቺ ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ሊፈቱት ይችላሉ። በህገመንግሥት ላይ ግን የዚያን ያህል የትርጉም ልዩነት አይፈጥርም። በዓለም ላይ ያሉት ህገመግሥቶች ተጠቃለው በሁለት ጎራ ከመከፈል አያመልጡም። ዲሞክራሲያዊ ህገመንግሥቶች ወይም ኢዲሞክራስያዊ የአባገነን ህገመንግሥቶች ተብሎ ከመመደብ ውጪ ሌላ ካታጎሪ የለም። ማንም አዋቂ የህግ ተርጓሚ ቢመጣ የአሜሪካ የፈረንሣይ የጀርመን የመሳሰሉትን ታዋቂ ዲሞክራቲክ አገሮች ህገመንግሥትን የአምባገነኖች ነው ብሎ ሊተረጉመው አይችልም። ምክንያቱም በነዚህ ሁለት ዓይነት ማለትም የሕዝብና የአምባገነኖች ህገመንግሥት መሃከል በሦስት ጉዳዮች ላይ መሠረታዊ ልዩነቶች አሉ።

አንደኛ፡- በአምባገነኖች ህገመንግሥት ሥልጣን ተጠቃልሎ የተከማቸው አንድ ቦታ ሲሆን፣ በዲምክራቲክ አገሮች ደግሞ ሥልጣን በህግ አውጪው በህግ አስፈጻሚውና ፍርድ ሰጪው መሃከል ተከፋፍሎ የተቀመጠ ነው።

ሁለተኛ፡- በኢዲሞክራሲያዊ ህገመንግሥቶች ዳኞች ነፃ አይደሉም። በዲሞክራቲክ አገሮች ግን የዳኞችን ነፃነት የሚጠብቅ አንቀጽ ብቻ ሣይሆን መካኒዝም በመፍጠር ሕዝቡ ፍትህ እንዲያገኝ ያደርጋል።

ሶስተኛ፡ የዲምክራቲክ አገሮች ህገመንግሥትን እንደዘበኛ ሆኖ የሚጠብቀው ልዩና ነፃ የሆነ የህገመንግሥት ፍርድ ቤት አለ። አምባገነን በሚገዙአቸው አገሮች ግን ይህ ይህ ፍርድ ቤት የለም። ቢኖርም ነፃ እና ገለልተኛ ሆኖ የተዋቀረ አይደለም።

በእነዚህ ሦስት ምክንያቶች ምክንያት የኢትዮጵያ ኢሕአዴግ ህገመንግሥት ከአምባገነኖች ህገመንግሥት ጎራ ይመደባል። ጉዳዩን በዝርዝር ስናየው የሚከተለውን ይመስላል።

1. በአንቀጽ 50 ቁጥር 3 ላይ "የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን አካል የፌዴራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው" ይላል። ይህ ዘዴ (ALL POWER TO THE SOVIETS) በሚለው የቀድሞዋ ሶቪየት ህብረት መርህ መሠረት ፤ ሥልጣንን ጠቅልሎ በአንድ ፓርቲ ሥር፤ ተያይዞም በፓርቲው መሪ ቁጥጥር ለማስገባት የተደረገ የኮሚኒስቶች ያረጀ ያፈጀ ዘዴ ነው። ዲሞክራቲክ አገሮች ሥልጣን አንድ ቦታ እንዳይከማች የፈለጉበት ምክንያት  አንድ ቦታ ሲከማች በአንድ ግለሰብ እጅ የመውደቁ እድል ሰፊ ነው። ያ ደግሞ ABSOLUTE POWER ይፈጥራል። ABSOLUTE POWER ደግሞ ያባልጋል ብለው ያምናል። ለዚህ ነው ABSOLUTE POWER CORRUPTS ABSOULUTELY የሚለው የLORD ACTON ጥቅስ ዝነኛ ጥቅስ የሆነው።
2. በአንቀጽ 79 ቁጥር 4 መሠረት ደግሞ፣ በጠቅላላ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ዳኞች በሙሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በፈላጭ ቆራጭነት ተቆጣጥሮ እንዲመራ ተደርጎ የተዋቀረ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አለ። ይህ ጉባዔ በማን እንደተሾመ፣ ስንት አባላት እንዳሉት፣ ለስንት ጊዜ እንደሚቆይ፣ ሆን ተብሎ ባልተገለጸ ሁኔታ እንዲዋቀር ተደርጎ፣ ኢሕአዴግ በዚህ ጉባዔ መሣሪያነት ጠቅላላ ዳኞችን እንድያሽከረክር ተመቻችቶ የተቋቋመ ነው።
3. ማንኛውም ህገመግሥት እንድዘበኛ ሆኖ የሚጠብቀው ወይም ህገ መንግሥቱን ከሚጥስ ማንኛውም ኃይል የሚከላከለው ነፃ ካውንሲል ወይንም ፍርድቤት ሊኖረው ይገባል በለናል። የህግ አዋቂዎች ሲናገሩ ይህ ዓይነት ጠባቂ ፍርድ ቤት የሊለው አገር፤ ህገመንግሥት እንደሌለው ይቆጠራል ይላሉ። አሜሪካን ውስጥ ይህን የጥበቃ ዘበኝነት ሥራ በዋነኛነት የሚሰራው ሱፐርም ኮርት ነው። ኢትዮጵያም ውስጥ ለስሙ ለዚህ ተግባር የተቋቋመ አንቀጽ 82 ቁጥር 2 የተጠቀሰ "የህገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ" አለ። የዚህ ጉባዔ አሥራ አንዱም አባላቶቹ የሚሾሙት በኢሕአዴግ ነው።  ስለዚህ ይህ ማለት ኢሕአዴግ የጣሰውን የሕዝቦች ህገመንግሥታዊ መብትን ለማስከበር ፤ ከሳሽ ተቃዋሚ ሃይል ቢመጣ፣ ጉዳዩን የሚመለከተው ራሱ ኢሕአዴግ ያቋቋመው ኮሚቴ መሆኑ ነው ማለት ነው። ልጁ ቀማኛ አባቱ ዳኛ ማለት ይህ አይደለምን?

እንግዲህ ዶክተሩ ይህንን ሥልጣን ላይ ለዘላለም ለመወዘፍ ያቀደ ድርጅት ይዘው ነው ወደ ዲሞክራሲ ሊያሸጋግሩን ቃል የሚገቡት። ምናልባት ዶክተሩ ድርጅቱን ሊለውጡት ነው ያሰቡት ብሎ ተስፋ ያደረገ ግለሰብ ካለ ድርጅቱን ለመለወጥ ድርጅቱ በሁለት እግሩ የተመረኮዘበትን ህገመንግሥቱን   መለወጥ ሊኖርባቸው ነው። ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ድርጅቱንና አሁን ያለውን ህገመንግሥት እንደሚቀበል ያሳወቀ መሪ ደግሞ ሥልጣኑን ሲረከብ ቀኝ እጁን አውጥቶ ሕገመንግሥቱን ሊጠብቅና ሊያስጠብቅ ቃለመሃላ የፈጸመ መሪ እንዴት አድርጎ አዲስ የመለወጥ ፈላጎት እንደሚፈጥር አይገባኝም።

በዚያ ላይ የኢሕ አዴግ ሌላው ጥንካሬው ሚዛናዊ ባልሆነ መድረክ ያጠራቀመው የስድስት ሚሊዮን አባላቶች ቁጥር ( በድርጅቱ ስሌት) ነው። በተጨማሪም ኢትዮጵያ ካሏት 3500 ሚሊየኔሮች ውስጥ በግምት 80% ራሱ ኢሕአዴግ ወልዶ፣ በአድልኦ እና በሙስና ያሳደጋቸውና ፤ አዘጋጅቶም ከጎኑ ያሰለፋቸው አባላቶችና ደጋፊዎች አሉት። ይህን ሃይል ከበታተነ ተቋዋሚዎች ለቃቅመው ሊወስዱበት ይችላሉ። ስለዚህ ሳይበትን ሳያንጠባጥብ መቀጠል ይፈልጋል ብዬ አምናለሁኝ።  አቅፎአቸው መቀጠል ከፈለገ ደግሞ የድሮውን አሠራሩን ብዙም ሳይለውጥ ጠገንገን ብቻ አድርጎ መቀጠል ሊኖርበት ነው።

በነዚህ ምክንያቶች ኢሕአዴግ ወደ ዲሞክራሲ ሊያሸጋግረን የሚችል ድርጅት አይደለም ማለት ነው። እንግዲህ ከዚህ ውጪ የሚቀረን የዶክተር አብይ  የተስፋ ቃል (ፐሮሚስ) ብቻ መሆኑ ነው። ዶክተር አብይ ቃላቸውን ለመጠበቃቸው ምን ማስተማመኛ አለ? ዶክተር ስለሆኑ? ሃይማኖተኛ ስለሆኑ? በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሃይማኖተኛ ሰዎች ቤተክሪስታያኖቻቸውን ወይንም ከነጭራሹ ሃይማኖታቸውን ጥለው የሚሄዱበት አንዱ ምክንያት የሃይማኖት መሪዎቻቸው ውሸት አስከፍቷቸው አይደለምን? ስለዚህ የሰነቅነው የማያስተማምን አጠራጣሪ ተስፋ ነው ማለት ነው። ያለን አስተማማኝ አማራጭ ሕዝባዊ የሆነውን ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት መመሥረት ነው። ለዚህም እንዲበጅ መጀመሪያ ያእርቅና የሠላም ጉባዔ ይጠራ ። ይህን ደግሞ ለማድረግ ተቋዋሚ ፓርቲዎች ዶክተር አብይን መጠበቅ የለባቸውም። ራሳቸው ድርጅቶቹ ተሰብስበው ጉባዔ መጥራት ይችላሉ። ቀሪው አገር ወዳድ ኢትዮጵያ ሁሉ በቁሳቁስና በገንዘብ መርዳት አገራዊ ግዴታ ነው እላለሁ።

አሁንም ለዘላቂ መፍትሄ ጊዜያዊ ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም!!

መከበብ ንጉሤ
ከምዕራብ አሜሪካ